ህዳር 12 ቀን 2002 ዓ.ም

# ከኢ.ሕ.አ.ፓ፣ ምን ፤ እንማራለን!
# እስቲ ትንሽ ስለ ኢሕአፓ - ከዓባይ ወንዝ በጭልፋ

ከአያልነሽ

## ኢሕአፓ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ!
## ልሣን፥ ዴሞክራሲያ!
## ራዲዮ፥ ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ!
## ድረ-ገፅ፥ www.eprp.com

ኢሕአፓ (የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ) የተመሠረተው በ1964 ሚያዚያ፤ በኢትዮጵያ በይፋ የታወጀው ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም ነው - ከዛሬ 35 ዓመት በፊት መሆኑ ነው። ይህ ድርጅት ራሱን ለሕዝብ ይፋ ከማድረጉ በፊት በመላ ኢትዮጵያ ሞልቶ ይንተከተክ የነበረው የህዝብ ብሶት ገንፍሎ እስኪወጣ ድረስ ውስጥ - ለውስጥ (ከ1964 - 1966 ዓ.ም) በሕቡዕ በህዝቡ መኃልና በሕዝቡ ውስጥ ሆኖ ራሱንና ሕዝቡን ሲያደራጅ ቆየ። በኋላም በነሐሴ ወር 1967 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱን ኢሕአፓ ብሎ በይፋ አስተዋወቀ - ልብ በሉ! .... ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም። የፓርቲውንም ፕሮግራም በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ቀንና በአንድ ሌሊት በአባላቱ አማካኝነት ለሕዝቡ አሰራጨ። አከታትሎም የድርጅቱን አቋምና የተመሠረተበትንም የመሠረት ድንጋይ የፓርቲው ልሣን በሆነው ዴሞክራሲያ በሠፊው አብራርቶ ገለጠ፤ ነሐሴ 26/1967። ይህ ወቅት መላ የኢሕአፓን አባላትና ወዳጆቹን ያስደሰተና በወታደራዊው አገዛዝ (ደርግ) ሠፈር ደግሞ፣ ከፍተኛ ድንጋጤን የፈጠረ ነበር። ኢሕአፓ የተመሰረተው በሕዝብ የብሶት እንባ ላይ ስለነበርም አመሠራረቱ ከሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄ ጋር መቆራኘቱ የሚጠበቅ ነው። ስለሆነም የድርጅቱ የመሠረት ድንጋይ የተጣለውና የተገነባው ከህዝብ ከታች ወደላይ፣ በህዝብ ልጆች የተቃጠለ ፍቅርና የሕይወት መስዋዕትነት ድልዳል ላይ ነው። ብዙኃኑ ወጣቶች ደግሞ ያኔ የትግሉ ዋና ሞተር ነበሩና ይህንን ድርጅት ለመቀላቀልም ጊዜ አልወሰደባቸውም።

ኢሕአፓ... እንደወጣቱ ሁሉ በኢትዮጵያ ደረጃ የግፍ እንባ ያፈሠሠውና በሐገሩ ምድር የበይ ተመልካች በመሆን ለዘመናት በችግርና በረኃብ ሲለበለብ በቆየው ብዙኃኑ ኢትዮጵያዊ - በሠራተኛው፣ በአስተማሪው፣ በተማሪው፣ በጭቁን ወታደሩ ክፍልም፣ ከፍተኛ ድጋፍን አግኝቷል። ኢሕአፓ ድርጅታችን ነው ብለውም በኢሕአፓ ጥላ ሥር ተሰልፈው "ኢሕአፓ ያሸንፋል" እያሉ፤ ለአላማቸው በመጽናት ከሞት ጋር ትንቅንቅ ገጥመውና ሞትን ንቀው ሕይወታቸውን በመስጠት መስዋዕት ሆነው ያለፉት አያሌ ናቸው። ኢሕአፓ እንዲህ ዓይነት ጀግኖችን በሥሩ እንዲሠለፉ ሲያደርግ....እንደአሁኖቹ "ዘመናዊ" ነን ባይ ፖለቲከኞች፣ በገንዘብ እየደለለ ሳይሆን..."ለመብታችንና ለነፃነታችን" የሚታገልና የሚያታግል ድርጅት ነው ብለው የተሠለፉበት ድርጅት ኢሕአፓ፣ እንደ እነ ተስፋዬ ደበሳይ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባል፣ ጓዶቹንና ድርጅታቸው ኢሕአፓን ለማዳን፣ የሞት ፊታውራሪ ሆኖ ሕይወቱን ያህል ወድ ነገር ሲሰዋ ተመልክተው ነበር።

በዚያን ወቅት አብዛኛው አርሶ አደር/ገበሬም የሚኖርበት ሁኔታ ከእጅ ወደ አፍና የመሬቱ ባለቤት ካለመሆኑም ሌላ ሕይወቱ በአሳዳሪው እጅ የወደቀበት ሁኔታም ስለነበር ትግሉን ተቀላቅሎ መስዋዕት ለመሆን የተዘጋጀና የቆረጠ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ከያኔ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በኢሕአፓ ላይ (በባላንጣዎቹ እንደሚወራበት) ያ ሁሉ ወጣት በኢሕአፓ ሥር ተጠልሎና

ተቀላቅሎ የታገለውና መስዋዕትነትን የከፈለው (ዛሬም ይህንኑ የሚያረገው) ለ"ሥልጣን " ሳይሆን፣ ከልብ ለመነጨ የሕዝብን ትግልና ተጋድሎ ለመታደግና፣ ሞቶም ለሕዝብና ለሐገሩ ኢትዮጵያ፣ ያለውን ፍቅር ለማሳየት ነበር፤ ነውም። ይህንን ደግሞ በተጨባጭና በግብር ሥርተው፣ በሞታቸው ፍቅርን የመግለፃቸውን መስተጋባር እውን በማድረጉ ረገድ፣ ከኢሕአፓ ወዲያ ላሣር ቢባል ማጋነን አይሆንም።

የኢሕአፓ አባላት በሞላ ከከፍተኛ አመራር ጀምሮ በየእርከኑ በኃላፊነት ቦታ ተመድበው የሚሠሩትን ጨምሮ፣ በዚህ በድርጅታቸው ውስጥ ተሰልፈው ውድ የሆነውን ሕይወት ለመክፈል ሲነሱ፤ እይታቸው የቅርብ ዓላሚ ሆኖ ሳይሆን የሩቅ ተላሚ፣ የእምነታቸው ዚቅ ጥልቅ፣ የኃሳብቸው ነቁጥ ደግሞ ትልቅ....ነውና ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በፍቅር ማንኛውንም ዓይነት መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጁና ከፍለውም በተግባር ያሳዩ ናችው። ይህንን ሐቅ አሌ የሚል አለ?

ኢሕአፓ መሪ የለውም አመራር እንጂ። በኢሕአፓ የትግል ታሪክ ውስጥ፣ ኢሕአፓ በአንድ መሪ ተመርቶ አያውቅም። በታሪኩ ኢሕአፓ የሚመራው በአባላቱ ነው። የኢሕአፓ መሪ ድርጅት-ፓርቲው ኢሕአፓ ነው። በኢሕአፓ ውስጥ እያንዳንዱ አባል የፓርቲው መሪና የፓርቲው አምባሳደር ነው። በኢሕአፓ ውስጥ ከታች እስከ ላይ የከፍተኛ አመራር ድረስ በእየርከኑ ተመድበው የሚሰሩት በሙሉ የሚሰጣቸው ድርሻ የሥራ ኃላፊነት እንጂ ሹመት አይደለም። በኢሕአፓ ውስጥ በኃላፊነት ተመድቦ የሚሰራው ሁሉ የተጣለበትን ኃላፊነት ደግሞ በግዴታ መወጣት አለበት። የኢሕአፓ አባላት የሕዝብ መሠረታዊ ጥቅሞችን ያስቀደሙና ለሕዝብ ሉዓላዊነት ዕውን መሆን የቆሙ ግለሰቦች ሲሆኑ፤ እነዚህ አባላት በሙሉ ድርጅቱን የሚቀላቀሉት ደግሞ በፈቃዳቸው ነው። እንዲህ ዓይነት አባላት በመሆናቸውና በፈቃዳቸው ገብተው እንደሚታገሉት ሁሉ በአንፃሩም በፈቃዳቸው የሚሠናበቱበትን ሙሉ መብትም በድርጅታቸው ሕገ ደንብ ውስጥ ደንግገው አስቀምጠዋል። ይህንንና መሰል ደንቦችን በሕገ ደንብ ውስጥ ቀርጾ ሲያስቀምጥ ድሮ ድሮ ከዛሬ 35 ዓመት በፊት በድቅድቅ ጨለማው ወቅት ነበር። ያኔ ትግል ሲጀምር ማለት ነው። ስለሆነም......ዛሬም ድረስ ይህን መብት የእያንዳንዱ አባል መብት ነው።

አንዳንዶች እንደሚሉት ኢሕአፓ ትግሉን ሲታገል እንዲያው ዝም ብሎ ዕድሜ ልኩን ለመታገልና እንደሚሉትም ሁሌ "መቃወም" ስለሚፈልግ፣ ወይንም "መታገልን" እንደሥራ ስለቆጠረው አይደለም። ምናልባትም ኢሕአፓን እንዲህ የሚሉት ኃይሎች ወይንም ግለሰቦች "ትግል" በሚለው ጽንሰ ኃሳብ ላይ ዛሬም ቢሆን የተንሸዋረር ዕይታ ያላቸው መሆናቸውን አመላካች ነው። በመሠረቱ ትግል ያውም የሕዝብ፤ ለመብቱና ለማንነቱ የሚያደርገውን ዕልህ አስጨራሽ ተጋዳሎን በዚህ ዓይነት፤ በትርፍና ኪሳራ ስሌት ተመልክተው የሚተቹ ካሉ በርግጥም ትግልን እንደቀልድ የሚያዩ ናቸው። አንድ ሕዝብ በነፃነት የማሰብ የተፈጥሮ ስጦታውን ተነጥቆ ነፃነቱን ካጣና አሳልፎም ከሰጠ የነፃነትን ተቃራኒ "ባርነት" ተቀብሏልና፤ "ነፃነት" ስለሚባለው ጽንሰ ኃሳብ የሚሰጠው ትንታኔ የባርነትን እሳቤ ይሆናል ማለት ነው። ለዚህም ነው ጭቆናና ግፍ እስካለ ድረስ ትግል አይቀሬ ይሆናል የሚባለው። በመሆኑም ኢሕአፓ፣ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እስካልሆነ ድረስ የጀመረውን ትግል ለማቆም አይግደድም - ይልቁንም የትግሉን አድማስ ይበልጥ እያቀጣጠለ የትግሉ አውራ ሆኖ በተጠንቀቅ ላይ ይገኛል። ትግል ደግሞ የነፃነት ተጋድሎ እንጅ የቅንጦት ጨዋታና የጊዜ ማሳለፊያ እንዳልሆነ ቢያንስ ለኢሕአፓ....ከምንም በላይ ግልፅ ነው። ምክንያቱም የሰው ሕይወት ይቀጠፍበታልና ነው። ኢሕአፓ ደግሞ የአንድ ሰው ሕይወት ያለ አግባብ እንዲጠፋና እንዲያልፍ አይፈልገም፤ አይመኝምም። ደግሞ ለአፍና አልኩ ለማለት ሳይሆን ከምርም የሚያምንበት፣ የመቆሚያው ምሶሶ በመሆኑ ነው። ለኢሕአፓ አንድ ሰው ማጣት ብዙ ሰው እንዳጣ ...ነው የሚቆጥረው። ለኢሕአፓ የአንድ ሰው ሕይወት በጣም በጣም ውድ ነው። ነፃነትንና ያለተሸራረፍ መሉ የዴሞክራሲ መብቶች ባለቤት ለመሆን የሚደረገው የሕዝብ ትግል ደግሞ በሠዓት፣በቀናት፣በወራት፣በዓመታት ተተምኖ የሚጀመርና የሚጨረስ አለመሆኑን ተረድቶ

ለተነሳው ኢሕአፓ.... የትግሉ አልፋ ኦሜጋ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እስኪሆን ድረስ ወስኖ የገባበት ለመሆኑ አያጠያይቅም።

ኢሕአፓ የሚታገልበት የመሠረት ድንጋይ የሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ማግኘታው ነውና፤ ዛሬም ቢሆን ከዛሬ 35 ዓመት በፊት የተነሳበትን ያን እምነቱንና ቃሉን ለመፈፀም ዋስትና ወይም ቃል የሚገባው ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው። ተጠያቂነቱም ከፍ ሲል ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ዝቅ ካለ ደግሞ ለኢሕአፓ ነው። ኢሕአፓ ትግል ሲጀመር ለመታገል ማንንም ፈቃድ አልጠየቀም። ይልቁንም ራሱን ለመስዋዕትነት አዘጋጅቶ ከሕዝብ ጎን ቆሞ፣ የሕዝቡን ቃል ሊፈጽም ታጥቆ ተሰለፈ እንጅ። የኢሕአፓ አባላት በሙሉ እንደ አያት ቅድም አያቶቻቸው ለሃገራቸውና ለሕዝባቸው ያላቸውን ቀናዒነት ሲያሳዩ በእርግጥ በሕይወታቸውና በደማቸው ታሪክ ጽፈው ለማለፍ ነውና ይህንንም "ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል" እያሉ በሕዝባቸው ማኃል ሞትን ያህል አስፈሪ ነገር ሞተው አሳይተዋል። በእርግጥም የኢትዮጵያ ሕዝብ አሸናፊ ነው ብለዋልና ሕዝባችን ደግሞ ይህንን አሸናፊነቱን በተደጋጋሚ ለባዕዳንም ጭምር አሳይቷል፣ አረጋግጧል። በ1966 ዓ.ም የየካቲት አብዮት ወቅትና አሁን በቅርቡ ደግሞ በ1997 ዓ.ም የግንቦት ምርጫ ወቅት የተደነቀ ገድሉን ፅፎ አልፏል! በእርግጥም ህዝብ አሸናፊ ነው።

ኢሕአፓ ይህንን ያህል ፅናት ይዞ እስከአሁን ለመቀጠል እንዴት ቻለ..? ለዚህ ጥንካሬውና ኣይበግሬነት አብነቱ ምንደን ነው?

.......ይቀጥላል!

## የህዝብ ድምፅ ይከበር! የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ
## ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

ቸር ይገጠመን

November 21/2009